# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 47 ሚያዚያ 1 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

.....የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን ወይንም የመንግስት ባለስልጣን መሆን በራሱ በሞራል ያስጠይቅ እንደሆነ እንጂ በፍርድ ቤት ደረጃ ያውም በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚያስጠይቅ አይደለም፡፡ ተጨባጭና ሙሉ ማስረጃ ያለባቸው ሰዎች ብቻ ነው የሚጠየቁት

**ርዕስ አንድቀፅ**

## በመለስ ዜናዊ ላይ የቀረበው የዘር ማጥፋት ውንጀላ በወያኔ ኢህአዴግ ቤት ሽብር መፍጠሩ ተገለጸ

አምባገነኑ ዘረኛ መለስ ዜናዊ፣ በዘር ማጥፋት እንዲከሰስ የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን የሚከታተተለው አለም አቀፍ ድርጅት በመለስ ዜናዊ ላይ ክስ እንዲመሰረት ጥያቄ መቅረቡ በወያኔ ኢህአዴግ አባላት ከታወቀ በኋላ በድርጅት ውስጥ ሽብር መንገሱን የግንቦት 7 ምንጮች አረጋገጡ፡፡

በወያኔ ኢህአዴግ ውስጥ የተነሳው ሽብር እንደ አበላቱ የስልጣን ደረጃ የተለያያ ነው፡፡ ከመለስ ጋር የቅረብ የስልጣን ግንኙነት ያላቸው ከመለስ ጋር በዘር ማጥፈት እንከሰሳለን የሚል ስጋት ገብቷቸዋል፡፡ የተራው አባል ጭንቀት መለስና የድርጅታቸው ከፍተኛ ባለሰልጣናት በወንጀል ተከሰው ለእስር የሚዳረጉ ከሆነ አኛን ምን ይውጠናል የሚል እንደሆነ ታውቋል፡፡

ይህ በመለስ ዜናዊ ላይ የቀረበው የዘር ማጥፋት ክስ በአገዛዙ ወታደራዊና የሲቪል ባለስልጣናት አካባቢም ሌላ ጭንቀት ቀስቅሷል፡፡
<<መለስ የዘር ማጥፋት ክስ ቀርቦበት ባላበት ሁኔታ እንዴት የጠቅላይ ሚኒስቴርነት ስራውን እንደልቡ ተነቀሳቀሶ መስራት ይችላል?

በተለይ ይህ ክስ እንዲቀርብ መጠየቁን የሚያውቁ የምእራብ መንግስታት መለስን ለማነጋርና ለአገዛዙ ከእዚህ ቀድሞ እንደሚያደርጉት ድጋፍ ለመስጠት ፈቃደኛ ይሆናሉ ወይ?>> የሚሉ ጥያቄዎች ማንሳቸው መጀመራቸው ታውቋል፡፡

አንዳንዶቹ ባለስልጠናት <<የአለም አቀፍ ፍርድ ቤቱ በመለስ ላይ ክስ አቅርቦ፣ በሱዳኑ ፕሬዚደንት ላይ እንዳደረገው እጁን ይዛችሁ አስረክቡ የሚል ማዘዣ ቢያወጣ ምን እንሆናለን? ሱዳን አላስረክብም ብትል የምእራብ ድጋፍ የማያስፈልጋት ሃገር ስለሆነች በነዳጅ ሽያጭ መኖር ትችላለች እኛ ግን ያለ ምእራብ መንግስታት እርዳታ አንድ ቀን ማደር የማንችለው ምን እንሆናለን? >> በሚሉ የጭንቀት ጥያቄዎች መወጠራቸውን እነዚሁ የውስጥ ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቀዋል፡፡

ለኢህአዴግ ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ «በመለስ ላይ ይህ ክስ መመስረት የወያኔ ባለስልጣናት መለስን መዳፈር እንዲጀምሩ የሚያደርግ፣ ይህ ግለሰብ ሁላችንም ይዞ ገደል ከመግባቱ በፊት አንድ ነገር ማድረግ ይገባናል የሚሉ ቡድኖችን የሚፈጥር እንደሆነና መለስ እንደነፍሱ የሚወዳት ሰልጣን ከእጁ ልታፈተልክ የሚችልበት ሁኔታ በቀላሉ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ የመለስ መጨረሻ መጀመሩን የሚጠቁም ይሆናል» ብለዋል፡፡

## የነጻው ፕሬስ አባላት በሽብርተኝነት ህግ ላይ ምንም አይነት ትንታኔና ዘገባ እንዳያቀርቡ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው፡

የግንቦት ሰባት ሬዲዮ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ እንደዘገበው አምስት የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ባለፈው ሳምንት ወደ ፌዴራል ፖሊስ እና ደህንነት ቢሮዎች ተጠርተው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል። ጋዜጠኞቹ ማስጠንቀቂያ እና ማስፈራሪያ የተሰጣቸው በቅርቡ የተረቀቀውን የጸረ ሽብርተኝነት ህግ አስመልክቶ በጋዜጦቻቸው ትንታኔ እና ዘገባ በማቅረባቸው እንደሆነ ታውቋል። በእለቱ ከዚህ በኋላ ረቂቅ ህጉን በሚመለከት ምንም አይነት ትንታኔና ዘገባ እንዳያቀርቡ ተነግሯቸዋል። ጋዜጠኞቹ የተለያዩ ረቂቅ ህጎች ላይ ሙያዊ ትንታኔ ሲሰጡ እና ለህዝቡም መረጃ ሲያቀርቡ መቆየታቸውን አስታውሰው አሁን በዚህኛው ህግ ላይ ለምን ትንታኔም ሆነ ዘገባ ማቅረብ እንደማይቻል እንደተከለከሉ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንና የደህንነቱ መ/ቤት በተላኩ ወኪሎች "ገና ባልጸደቀ ህግ ላይ ምንም ትንታኔ መስጠት አትችሉም ?" የሚል መልስ እንደተሰጣቸው ለማወቅ ተችሏል።

(ወደ 4ኛው ገፅ ይዞራል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የቡድን ሃያ መሪዎች የእርዳታ ገንዘብ የሚዘርፉ አምባገነን መሪዎችን ለመቆጣጠር ስምምነት ላይ መድረሳቸው መለስ ዜናዊን አስበረገገ።

የቡድን ሃያ አገራት መሪዎች የእርዳታ ገንዘብ እየዘረፉ ለግል ጥሪታቸው የሚያከማቹ አምባገነን የታዳጊ አገሮች መሪዎችን ለመቆጣጠር ስምምነት ላይ መድረሳቸው መለስ ዜናዊን አስበረገገ። በዚሁ ምክንያትም ከስብሰባው ቦኋላ አፍሪካን ወክሎ እንዲናገር የተያዘለትን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰርዞ እንደፈረጠጠ ብላክ ስታር ኒውስ የተባለ ጋዜጣ ዘገበ::

ባለፈው ሃሙስ በሎንድን ከተማ ለአንድ ቀን ተካሂዶ በነበረው የቡድን 20 ስብሰባ ላይ የተሳተፉት ታላላቅ የአለም መሪዎች በስብሰባቸው ወቅት ከደረሱባቸው ስምምነቶች አንዱ አፍሪካ በዓለም አቀፉ የገንዘብ ቀውስ እንዳትጠቃ ለመከላከል ወደ 250 ቢሊየን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ በእርዳታ እንድታገኝ ለማድረግ ነው ። ነገር ግን የአንዳንድ አፍሪካ አምባገነን መሪዎች ከሚስኪኑ ህዝባቸው ገንዘብ እየዘረፉ ውጭ አገር ባሉ ባንኮች በድብቅ ወደከፈቷቸው የግል ሂሳብ የማሸሻቸው ጉዳይ ለአፍሪካ የሚሰጠውን እርዳታ ትርጉም የለሽ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ድህነትን ለማባባስ ዓይነተኛ ምክንያት በመሆኑ ከምንም ጊዜ በላይ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱና ሃብታሙ አገሮች ከግብር ከፋይ ህዝባቸው እየተቀበሉ ደሃውን ለመርዳት የሚሰጡት ገንዘብ የጥቂት ሌቦች መጠቀሚያ መሆኑን ለማስቆም እስከ አሁን የተዘረፈውን ገንዘብ ለማስመለስም ሆነ ወደፊት ችግሩን ለማስወገድ እንዲቻል ፋይናንሻል ስታቢሊቲ ቦርድ የተባለ ተቋም በአስቸኳይ እንዲቋቋም ከስምምነት ላይ ደርሰዋል። የጀርመኗ ቻንስለር አንጄላ መርከል ይህን በተመለከተ ሲናገሩ፣ ከአሁን ቦኋላ "የገንዘብ ማሸሽ ዘመን አብቅቷል" ማለታቸው ተዘግቧል።

የደቡብ አፍሪካው ፕሬዚደንት ኪጋሌማ ሞትላንቴ ከስብሰባው ቦኋላ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች ውስጥ ይሄው የአንዳንድ አፍሪካ አምባገነኖች ከደሃው ህዝባቸው እየሰረቁ ወደውጪ አገር ሰለሚያሸሹ ገንዘብ ጉዳይ ሲሆን፣ ፕሬዚደንቱ በቡድን ሃያ ስብሰባ ላይ የተገኙት አፍሪካን ወክለው ሳይሆን አገራቸው በምጣኔ ሃብት ከደረሰችበት የዕድገት ደረጃ አኳያ ተጋብዘው መሆኑን በመጥቀስ አፍረካን ወክለው መናገር እንደማይጠበቅባቸው በማስረዳት ጥያቄያቸውን ለማን ማቅረብ እንዳለባቸው በፎርም ጠቆም አድርገው አልፈዋል። ከዚያ በኋላ ጋዘጠኞቹ እንደ ኔፓድ ሊቀመንበርነቱ አፍሪካን ወክሎ በስብሰባው ላይ የተገኘው መለስ ዜናዊ በሚኖረው ጋዜጣዊ መግለጫ ይህንን በተመለከተ መልስ ይሰጠናል ብለው ተንሰፍስፈው ሲጠባበቁ መለስ በድንገት ፕሮግራሙን ሰርዞ እንደተሰወረባቸው የብላክ ስታር ጋዜጠኛ አጋልጦአል::

(ወደ 4ኛው ገ\ፅ ዞሯል)

## በንግዱን ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ቀረጥ ጭማሪ የማድረግ የወያኔ ዕቅድ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ ከፍተና ድንጋጤ ፈጥሮአል

ወያኔ ከቀን ወደ ቀን እየተራቆተ እና እየተንኮታኮተ የመጣውን ምጣኔ ሀብቱን ለመደጎም በማሰብ በንግድ ማህበረሰቡ ላይ ሊጥል ያሰበው ከፍተኛ ቀረጥ የንግዱን ማህበረሰብ ቁጣ እንደቀሰቀሰ ተዘገበ።ከጥቂት ሳምንታት በፊት ከገቢዎችን እና ጉምሩክ ባለስልጣን ግብረ ሀይል የተለያዩ የግል ኩባንያዎችን ለሶስት አመታት የተገበያዩበትን፤እቃ ከውጪ ያመጡበትን እና አጠቃላይ ገቢያቸውን የሚገልጽ ሰንድ እንዲያመጡ መጠየቃቸው ታውቋል።

በግብረ ሀይሉ ውስጥ ያሉ ግለሰቮች በዘፈቀደ የፈለጉትን ያህል እንደሚያስከፍሉ ተገለጿል።ከ55 ኩባንያዎች በመዝገባችሁ ላይ ያሰፈራችሁትን እና የከፈላችሁት ልዩነት አለው በሚል ከ አራት እስከ አስር ሚሊዮን ብር እንዲከፍሉ መጠየቃቸው ታውቋል።

በተጣለባቸው ከፍተኛ ግብር እና ቅጣት ክፉኛ የተማረሩ አንድ ነጋዴ <<መንግስት የደረሰበትን የበጀት እጥረት እና የምጣኔ ሀብት ቀውስ እኔን ከቁመቴ በላይ እየቀረጠ ሊያካክስ አይችልም።ከዚህ በሓላ የምከፍለው አምስት ሳንቲም የለኝም።ከፈለገ ድርጅቴን ይውሰደው ።>ሲሉ ተደምጠዋል።

ወያኔ በአመት ከሚያስፈልገው 55ቢሊዮን አመታዊ በጀት 30ቢሊዮን የሚያክለውን ከግብር እሰበስባሉ ብሎ ህዝቡን ማስጨነቁ በአስከፊ ሁኔታ ከጨመረው የዋጋ ግሽበት ባሻገር ምናልባት ፊት የነሱት ምእራባዊያን አለቆቹ እርጥባን ካልወረወሩልኛ ባዶዬን ልቀር እችላለሁ ብሎ ፈርቶ ሳይሆን እንዳልቀረ ተገምቷል።

እንደ ኤፈርት ያሉት የወያኔ የንግድ ኢምፓየሮች እና ከወያኔ ጋር በተለያየ መንገድ ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች ግብር እንዲከፈሉ እንደማይገደዱ ሲታወቅ በተለይ ከምርጫ 97 በሓላ ወያኔ ጠምዶ የያዛቸው የመርካቶ ነጋዴዎች በመባል የሚታወቁት እና ከወያኔ ጋር የማያጨበጭቡ የንግድ ተቋማት በርካታ ግብር እንደተጣለባቸው ታውቋል።

## የውሸት ክምር መፍረስ ሲጀምር የሚያቆመው የለም፡፡

እነመለስ ለ18 አመት የገነቡት የውሸት ክምር በድንገትና ከሁሉም አቅጣጫ መፍረስ መጀመሩን ፍንትው አድርጎ ያሳየን ሳምንት ነበር ያለፈው ሳምንት፡፡ ለዛሬው በአንድ ነጥብ ላይ ብቻ እናተኩር፡፡ የነመለስ ወንጀል በአለም አቀፍ ደረጃ መውጣቱ በፈጠረው ትርምስና በሚኖረው ፖለቲካዊ እንደምታ ላይ፡፡

በአለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ዘርፍ መለስ የደረሰበት ውርደት ቀላል አይደለም፡፡ በተለይ ጄኖሳይድ ዎች የሚባለው ታዋቂው የሰብአዊ መብት ተሙዋጋች ድርጅት በነመለስ ላይ ምርመራ እንዲደረግ በኦፊሴል ያቀረበው ጥሪ በነመለስ ላይ ሽብር መፍጠሩ አይቀርም፡፡ የጊዜ ጉዳይ እንጂ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሚያስቀርብ መሆኑና ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ማስረጃ መሰብሰብ መጀመሩን ጄኖሳይድ ዎች ግልጽ አድርጎታል፡፡ ይህ ደግሞ ለነመለስ ድጋፍ የሚሰጡ የምእራባውያን አገሮችን አንገት ያስደፋ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ መለስ በዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲከሰስ በጄኖሳይድ ዎች የቀረበው ጥያቄ በአገራችን የወደፊት ፖለቲካ ላይ የሚኖረውን እንደምታ ተመልክተን ለዚያም እንድንዘጋጅ የሚጋብዝ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ሁለት ቁምነገሮችን በጥንቃቄ መመልከት ይገባል፡፡ የመጀመሪያው ይህ ወንጀል የሚመለከታቸው የወያኔ/ኢሕአዴግ ባለሙዋሎች እነማን ናቸው? ሁለተኛው የዚህ ክስተት የአሁኑና ዘላቂው የፖለቲካ እንደምታ ምንድን ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

በዘር ማጥፋትና በሰው ልጆች ላይ በተፈፀመ ወንጀል በወያኔ ኢሕአዴግ ውስጥ ሊጠየቁ የሚችሉት የትኞቹ የፓርቲ፤ የመንግስትና ወታደራዊ ባለስልጣናት ናቸው የሚለው ጥያቄ እንደነመለስና ሽመልስ ከማል በአንድ ሌሊት የሚፈበረክ አይደለም፡፡ በአንድ ቀንም ውስጥ ምስክር አሰልጥኖ (ያውም የቀሺም አይነት ስልጠና) የሚቀርብ አይሆንም፡፡ ለተከሳሽ መብት የበለጠ ቀናኢ ለሆነ የአለም አቀፍ ፍ/ቤት የሚቀርብ ክስ እንደመሆኑ ክሱም ሆነ ጥቆማው የማያወላውል ማስረጃ ይፈልጋል፡፡ ይህ ክስ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች በጣም በጥንቃቄ አበጥረው ያገኙአቸው ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው የሚሆነው፡፡ እንዲሁ እንደመለስ ከሳሾቹ ከኪሳቸው ክስ አውጥተው ‹ኢንተርሀምዌ› ብለው እንደማይወነጅሉ መቼም የታወቀ ነው፡፡ በወንጀለኛነት ሊከሰሱ የታሰቡት ግለሰቦች የነበራቸው የተሳትፎ አይነትና ጥልቀት ገና እየተመረመረ ነው፡፡ ቢሆንም ይህን የማስረጃ ማሰባሰብ ስራ ከሚሰሩ ሰዎች አካባቢ የሚደርሰው ተባራሪ ወሬ እንደሚያመለክተው ከሆነ በነኝህ ከፍተኛ ወንጀሎች የሚጠረጠሩት ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ አይደለም፡፡ ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታና የወንጀሉም ጥልቀት ይለያያል፡፡ በጥቅሉ ለሁሉም ግፎች ፖለቲካውንና መንግስትን በዋናነት የሚመሩት የኢሕአዴግ ስራ አስፈፃሚ አባላት በተለይም መለስ ዜናዊ በቁንጮነት ተጠያቂ መሆኑ ግልጽ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም፣ በያንዳንዱ ወንጀል ቢያንስ የሚከተሉት ሰዎች ላይ የማጣራት ሂደት እየተካሄደ እንደሆነ ጥቆማ ደርሶናል፤

ሀ. በጋምቤላ በተፈፀመው ጭፍጨፋ፡
1. ዐባይ ፀሀዬ (በጊዜው የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር የነበረ)
2. ዶ/ር ገብረአብ ባርናባስ (በጊዜው ሚኒስትር ደኤታ የነበረና በቦታው በመገኘት ጭፍጨፋውን ያስተባብር የነበረ)
3. ኮሎኔል ፀጋዬ (በጊዜው በቦታው የነበረው ወታደራዊ ሀይል አዛዥ)
4. ኡሞት አባንግ (አሁን የጋምቤላ ክልል አስተዳዳሪ)

ለ. በአዲስ አበባ ለተፈፀመው ጭፍጨፋ፡ (በመለስ ዜናዊ የሚመራው የጊዜው የአዲስ አበባ ኮማንድ ፖስት አባላት)
1. መለስ ዜናዊ (ጠ/ሚኒስቴር እና የኮማንዱ ሊቀመንበር)
2. ጌታቸው አሰፋ (በምክትል ሚኒስቴር ማእረግ፡ የሕዝብ ደህንነት መስሪያ ቤት ዋና ሀላፊ)
3. አባይ ፀሀዬ
4. ጄነራል ሳሙራ የኑስ (ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም)
5. አዲሱ ለገሰ (ም/ጠቅላይ ሚኒስቴር)
6. በረከት ስምኦን

ሐ. ለኦጋዴን ጭፍጨፋ (በፖለቲካው መሪነት ከሚጠየቁት በተጨማሪ)
1. ሜ/ጄነራል አብረሃ ወ/ማሪያም (ልዩ ስሙ ኳዋርተር፡ የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ)
2. ብ/ጄነራል ሙሉጌታ በርሄ (የምስራቅ እዝ ምክትል አዛዥ)
3. ኮ/ል ወ/ገብረኤል ባቤ (ልዩ ስሙ ወዲ ባቤ፡ የምስራቅ እዝ ምክትል አዛዥ)
4. ወዲ አንጥሩ በሚል የቅጽል ስም የሚታወቅ (የ 12ኛ ክ/ጦር ዋና አዛዥ)
5. ኮ/ል ፀጋዬ (ልዩ ስሙ ጀብጀብ፡ የ13 ኛ ክ/ጦር ዋና አዛዥ)
6. ብ/ጄኔራል ዮሀንስ (ልዩ ስሙ ጆን መድድ)
7. ኮ/ል ፀሀዬ (ልዩ ስሙ ፀሀዬ መንጁስ)
8. ኮ/ል አስቴር በሚል የቅጽል ስም የሚታወቅ (በጭፍጨፋው ከፍተኛ ተሳትፎ አለው የሚባል)
9. ወዲ ፈላንሳ በሚል የቅፅል ስም የሚታወቅ (የምስራቅ እዝ መረጃ መምሪያ ሀላፊ)

መ. በሶማሌ በተለይ በሞቃዲሾ ለተፈፀመው ጭፍጨፋ
1. ሜ/ጄነራል ስዩም ሀጎስ (የሶማሌ ግንባር አዛዥ)
2. ብ/ጄነራል ሙሉጌታ በርሄ (የአጋዚ ክ/ጦር ዋና አዛዥ)
3. ብ/ጄነራል ገብረ አድሀነ (ልዩ ስሙ ገብረ ዲላ የ 44ኛ ክ/ጦር ዋና አዛዥ)
4. ኮ/ል ገ/ዮሀንስ አባተ (ወዲ አባተ) (የአጋዚ ክ/ጦር ምክትል አዛዥ)
5. በኦጋዴን ጭፍጨፋ ላይ የተጠቀሰው ኮ/ል አስቴር በሚል የቅጽል ስም የሚታወቅ

እነኝህ በጠቅላላ 24 ሰዎች ማስረጃ እየተሰበሰበባቸው ነው፡፡ ከዚህ በላይ የሉም ለማለት ሳይሆን ለጊዜው ምርመራው ያነጣጠረው በነኝህ ሰዎች ላይ ነው ማለት ነው፡፡ ከነኝህ ውጭ በማስረጃ የተደገፈ ውንጀላ አለኝ የሚል ሰው ሁሉ ለሚመለከታቸው ሰዎች ማስረጃውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ልብ ሊባል የሚገባው የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን ወይንም የመንግስት ባለስልጣን መሆን በራሱ በሞራል ያስጠይቅ እንደሆነ እንጂ በፍርድ ቤት ደረጃ ያውም በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚያስጠይቅ አይደለም፡፡ ተጨባጭና ሙሉ ማስረጃ ያለባቸው ሰዎች ብቻ ነው የሚጠየቁት፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በአፅንኦት ሊታሰብበት የሚገባው የዚህ ክስተት የፖለቲካ እንደምታው ምንድን ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በእኛ አመለካከት ይህ ክስተት የነመለስን በውሸት ላይ የተካበ መንግስት ማብቂያ ጊዜ የታወጀበት ነው እንላለን፡፡ ጊዜው እነመለስ የቀረቻቸውን ትንፋሽ ላለማጣት የሚንፈራገጡበት ጊዜ መቃረቡን ያሳያል፡፡ በአንድ በኩል እነ መለስ ሲንፈራገጡ ብዙ አደጋ እንዳያደርሱ የምንከላከልበት በሌላ በኩል ደግሞ ስለወደፊቱዋ ኢትዮጵያ በጥንቃቄ የምንወያይበት ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ከበፊቱ ስህተቶቻችን ተምረን ይህንን እድል በትናንሽ ሽኩቻ እንዳናበላሽ ከፍተኛ ጥንቃቄ የምናደርግበት ወቅት እየተቃረበ ነው፡፡ ወቅቱን የነመለስ አገዛዝ ለኢትዮጵያውያን የመጨረሻው አምባገነን አገዛዝ የሚሆንበትና የኢትዮጵያውያን ውርደት የሚያበቃበት የምናደርግበት ሊሆን ይገባል እንላለን፡፡

የዚህን ጉዞ እርምጃ ከአሁኑ መጀመር አለብን፡፡ በግንቦት 7 አመለካከት እነኝህና ሌሎች በአለም አቀፍ ወንጀል የሚጠየቁ ሰዎችን ከሌሎቹ የወያኔ/ኢሕአዴግ ሰዎች ለይተን መመልከት ያስፈልጋል እንላለን፡፡ በማወቅ ይሁን ባለማወቅ የራሳቸውን እጣ ፈንታ ከነኝህ ወንጀለኞች ጋር አቆራኝተው ለሚያዩት በሙሉ ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ ማስተላለፍ እንወዳለን፡፡ የመለስና የቅርብ ባለሟሎቹ ጉዳይ የግዜ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ አብቅቶለታል፡፡ መለስና ጓደኞቹ ግን ከማያመልጡት ውድቀት ለማምለጥ በሚያደርጉት የአልሞት ባይ ተጋዳይነት የተነሳ ተጨማሪ ወንጀል ለመፈጸም አይመለሱም፡፡ በእዚህ ድርጊታቸው አንዱ ማድረግ የሚሞክሩት ነገር በርካታ የድርጅት አባላቶቻቸውን እንደነሱ ወንጀለኛ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ የወንጀለኛውን ቁጥር በማበራከት እጅ ላለመስጠት በቀቢጸ-ተስፋ መቅበዝበዛቸው አይቀርም፡፡ የኢህአዴግ አበላት ሊያውቁት የሚገባው ከላይ ከተጠቀስናቸውና በእነሱ ላይ ከሚጨመሩ በጣት ከሚቆጠሩ ወንጀለኞች ውጭ ሌላው የወያኔ /ኢህአዴግ አባል የሚሰጋው ምንም ነገር እንደሌለ ነው፡፡ በመሆኑም በእዚህ የመጨረሻ ሰአት እነመለስ በወንጀል በሽታቸው እንዳይለክፉት ብዙሃኑ የኢህአዴግ አባል ነቅቶ መጠበቅ አለበት፡፡ እነመለስ ዜናዊ በወንጀለኛነታቸው እጃቸውን ተጠምዘው ከሄዱ በኋላ የሚቀር ችግር ካለ በአገራችን ሊፈጠር ይገባል ብለን የምናምነው የእውነትና የእርቅ ውይይት ሊፈታው የማይቸለው ምንም ነገር አይኖረም የሚል እምነት አለን፡፡ በመሆኑም የግንቦት 7 ንቅናቄ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስር ላሉ የወታደርም ሆነ የሲቪል አገልጋዮች፤ «ከአሁን በኋላ ከእዚህ አገዛዝ ጋር መተባበሩ አያዋጣችሁምና ከአሁኑ ሚናችሁን ለዩ» በማለት ምክሩን ይለግሳል፡፡

ሃይለ ሀሳብ

ለተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ፡-ከጄኖሳይድ ዎች የተጻፈ ማመልከቻ
የአማሪኛ ትርጉም (በግንቦት 7 ድምጽ ዝግጅት ክፍል የተተረጎመ)

## ግልጽ ደብዳቤ ለተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር

ለዳኛ ናቫናተም ፒሌ

ለአቤቱታ ሰሚ ቡድን
የተባበሩት መንግስታት
የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤት
ክብርት ኮሚሽነር፡-

በዓለም ዙሪያ ያሉ የፍትህ ተሟጋቾች፣ የአለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ በሱዳኑ መሪ አማር አልበሽር ላይ የእስር ትዕዛዝ በማስተላለፍ ላለፉት ስድስት ዓመታት ዳርፉር ውስጥ እየተፈጸሙ ላሉት ግፎች በመጨረሻ ለተጠያቂነት እንዲቀርብ በወሰደው ጠንካራ እርምጃ እጅግ ተደስተዋል። በባሺር አመራር ስር፥ በዳርፉር እና በደቡብ ሱዳን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሱዳናያውያን ሊታሰብ የማይችል ጉዳት፣ ኢ-ፍትሃዊነት እና መከራ ቀምሰዋል።

አለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ የወሰደው እርምጃ፥ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህጎች በወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባርም እንደሚገለጹ በማረጋገጥ ለሰላምና ፍትህ ወዳዶች ተስፋን አለምልሟል። በዓለም ዙሪያ ላሉ ወንጀል ፈፃሚዎችም፣ በማንአለብኝነት የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች ለዘላለም እንደማይቀጥሉ መልዕክት ይልካል፡፡ በኢትዮጵያና ሶማሊያ ውስጥ በሰፊው እና በከፍተኛ ደረጃ የሰብዓዊ መብት ግፎችን በመፈጸም የተወነጀለው አገዛዝ መሪ የሆነው የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ቀድመው ለአልበሽር ከተከላከሉለት መሪዎች ውስጥ አንዱ የሆነበት ዋነኛው ምክንያትም ይህ ሳይሆን አይቀርም። ወንጀል ፈፃሚዎች ለተጠያቂነት እንዳይቀርቡ የሚከለክለውን ስር የሰደደና በመንግስት የተደገፈ ማን አለብኝነት እንዲያከትም የሚያደርግ ተመሳሳይ እርምጃ በአለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት ወደፊት ሊወሰድባቸው እንደሚችል እሱና በአገዛዙ ውስጥ ያሉ ጠንቅቀው ሳያውቁ አይቀርም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው አስከፊ የሰብዓዊ መብት ሁኔታ መጀመሪያ ያወቅሁት የአኟክ ጀስቲስ ካውንስል መሪ አባንግ ሜቶ (አሁን የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ መሪ) ጀኖሳይድ ዎች እና ሰርቫይቨርስ ራይትስ ኢንተርናሽናል የተባለው ድርጅት በታህሳስ ወር 1996 ዓ.ም በ424 አኟኮች ላይ በጋምቤላ ስለተፈጸመው የግፍ ግድያ ምርመራ እንድናደርግ ጥሪ ሲያደርግ ነው። አኟኮች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዳርቻ የሚኖሩ በቁጥራቸው ጥቂት እና የቆዳቸው መልክ ጠቆር ያለ ዘውጌ ቡድን ናቸው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሃይሎች እና ከሌላ ዘውጌ ማህበረሰባት የወጡ የሲቪል ሚሊሻ ቡድኖች አስቀድሞ የተዘጋጀ የስም ዝርዝር በመጠቀም የአኟክ መሪዎችን የጥቃት ኢላማቸው አድርገዋል፤ ከነዚህ መሪዎች ብዙዎቹ መንግስት እነሱን ሳያሳትፍ በመሬታቸው ላይ የነዳጅ ዘይት ቁፋሮ ለማድረግ ያለውን እቅድ የሚቃወሙ ነበሩ። “ዛሬ አኟክ የመግደያ ቀን ነው” በሚለው የሚሊሻዎቹ መፈክር ታጅበው፥ ሚሊሻዎቹም ጦር ገጀራ፣ ፋስ እና ጠብመንጃ በመጠቀም ያልታጠቁትን ሰዎች ሲገድሉ፣ አንዳንዴም “ከዚህ በኋላ የአኟክ ልጆች አይኖሩም” የሚል መፈክር እያሰሙ ሴቶቹን ይደፍሩ ነበር።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሃይል ተመሳሳይ ወንጀሎችን ወደፈጸመበት እና አሁንም መፈጸሙን ወደቀጠለበት በምስራቅ ኢትዮጵያ ወደሚገኘው ኦጋዴን አካባቢ እና ወደ ሶማሊያ እስከተላከበት እስከ 1998 ዓ.ም አጋማሽ አካባቢ ድረስ፣ በጋምቤላ ህገ-ወጥ ግድያዎች፣ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች፣ እንደ ወጡ መቅረት፣ የኑሮ መመሰቃቀል እና በሺዎች የሚቆጥሩ አኟኮች መሰደድ ቀጥሎ ነበር። ከሰብዓዊ መብት ወንጀሎቹ በስተጀርባ ማን እንዳለ ለማወቅ በጀኖሳይድ ዎች እና በሰርቫይቨርስ ራይትስ ኢንተርናሽናል በአኟኮች ጭፍጨፋ ላይ የተደረገው ምርመራ፣ ከኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት የመነጨ “የጸሃያማው ተራራ ኦፕሬሽን” የተባለ እቅድ እንደነበር ደርሶበታል።

በምርመራችን ላይ እና በዓለም ህግ የዘር ማጥፋት ወንጀልን በተመለከተ ባለን ልምድ ላይ በመመስረት፣ በጋምቤላ በአኟኮች ላይ የተፈጸመው ግድያ የዘር ማጥፋት ወንጀልንና በሰው ልጆች ስብእና ላይ የተፈጸመ ወንጀል መስፈርቶችን እንደሚያሟላ ድምዳሜ ላይ ደርሰናል። ሂውማን ራይትስ ዎችም ሁለት ምርመራዎችን አድርጎ በአኟኮች ላይ የተፈጸመው ወንጀል በሰው ልጅ ስብእና ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ትርጉም እንደሚያሟላ ደርሶበታል።
በኢትዮጵያ የፍትህ ተቋም ውስጥ ካለው ድክመት እና ዝቅጠት የተነሳ ሂውማን ራይትስ ዎችና በኛም ሪፖርት ውስጥ የተጠቀሱት የወንጀሉ ፈፃሚዎች ለፍርድ ቀርበው አያውቁም። ምንም እንኳ የዓለም አቀፍ ህግ ቢጣስም፣ ከአምስት ዓመት በፊት ለተፈጸሙት ለነዚህ ወንጀሎች ማንም ለተጠያቂነት አለመቅረቡ ብቻ ሳይሆን፤ ነገር ግን ከዚህ በከፋ ሁኔታ፥ ተመሳሳይ ወንጀሎች በሌላ የአገሪቱ ክፍሎች መፈጸማቸውን ቀጥለዋል።

በተከበሩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ምርመራ የተደረገባቸው ክስተቶች የተወሰኑት ናቸው፤ ነገር ግን በነሱም ቢሆን፣ የሚገኙት ማስረጃዎች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያሳዩት ወንጀሉን በማነሳሳትም ሆነ በማበረታታት፣ ወይም በሰው ልጆች ስብዕና ላይ የሚደረግ ወንጀል፣ ወይም የጦር ወንጀል እና የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ “ጸረ-ሰላም ሃይሎችን” በመዋጋት ስም በመፈጸም የኢትዮጵያ መንግስት እጅ እንዳለበት ነው።

እነዚህን እውነታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንደ ተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነርነትዎ በተላበሱት እርምጃ የመውሰድ ስልጣንዎ (*proprio motu* powers) ተጠቅመው፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ምርመራ እንዲደረግ እርምጃ እንዲወስዱ አጥብቄ እማጸንዎታለሁ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የማን አለብኝነት ባህል የተነሳ የእርስዎ ምርመራ ተገቢ ነው ብለን እናምናለን። የመብት ጥሰቶቹን ለመመርመር የሚያስችሉ በአብዛኛው በገለልተኛ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች በተደረጉ የምርመራ ሪፖርቶች ውስጥ የተሰባሰቡ ሰፊ ማስረጃዎች አሉ። ሽብርተኝነትን እዋጋለሁ እያለ የገዛ ህዝቡን በሚያሸብረው መንግስት ከሚያካሄደው ጨካኝ አፈና እና ስቆቃ የኢትዮጵያ ህዝብ እረፍትንና ቅን የሆነን ፍትህ ሲጠባበቅ ለረዥም ጊዜ ቆይቷል ብለንም እናምናለን። ለኦማር አልበሽር ቅርብ የሆነውን የኢህአዴግን አገዛዝ አንድ ማለቱ ወደ አፍሪቃ ቀንድ መረጋጋትን ሊያመጣ ይችላል።

እኛ በጀኖሳይድ ዎች እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ውስጥ ያለን፣ ወንጀሉ ከተፈጸመ ረጅም ጊዜ ቢያልፈው እንኳ፣ በተልዕኳችን መሰረት ፍትህን ለማስፈን ቆርጠን የተነሳን በመሆናችን፣ ይህንን ተግባር ለመፈጸም የሚያስችሎትን እገዛ ለማድረግ ፈቃደኞች ነን። ከዚህ በፊት የተካሄዱ ምርመራ ሪፖርቶች፣ አድራሻዎች እና ሌሎች መረጃዎች የሚፈልጉ ከሆነ ልናቀርብ ዝግጁዎች ነን።

የፍትህ ጠላት የሆነውን ማንአለብኝነትን ለመዋጋት እየሰሩት ስላሉት መልካም ስራ አመሰግንዎታለሁ። በሰው ልጆች ስብእና ላይ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች በነፃ እንዲመላለሱ ሊፈቀድላቸው አይገባም። ጀኖሳይድ ዎች፥ እነዚህ ወንጀሎች የከበደ ቅጣት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተጨማሪ መንገዶችን ከማፈላለግ አኳያ፣ ከሌሎች ጋር በመተባበር የራሱን አስተዋጾ ማድረጉን ይቀጥላል። አንዱ መንገድ፥ ከመንግስታት ጋር በመስራት እነዚህን ወንጀሎች የፈጸሙት ኢትዮጵያውያን ወደ ምእራባውያን አገሮች መግቢያ ቪዛ እንዳያገኙ ማድረግ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ በብዙ ምዕራባውያን አገሮች እየተደነገጉ ባሉ አዳዲስ ህጎች ተደግፏል። በተጨማሪም፥ ባሁኑ ጊዜ በካናዳ፣ በአውሮፓ እና በዩናይትድ ስተትስ ኦፍ አሜሪካ ክስ ለመመስረት በቂ የሆነ መረጃ የተገኘባቸው አዲስ ነዋሪዎችን ለፍርድ ማቅረብ እንዲችሉ ለየመንግስታቱ ስልጣን የሚሰጡ ህጎች አሉ። ምእራባውያን አገሮች ከዚህ በኋላ ለነዚህ ወንጀለኞች እንደ መደበቂያ ሆነው ሊያገለግሉ አይገባም።

በኢትዮጵያ በተፈጸሙት የዘር ማጥፋት፣ በሰው ልጆች ስብእና ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች እና የጦር ወንጀሎች ላይ ምርመራ እንዲደረግ እርምጃ እንዲወሰዱ የቀረበውን ይህን ጥያቄ ስለተመለከቱልን እናመሰግናለን። መልስዎን ለመስማት በጉጉት እንጠባበቃለን።

ከትህትና ጋር

ዶ/ር ግሬጎሪ ስታንተን
የጀኖሳይድ ዎች ፕሬዘደንት

**የነጻው ፕሬስ አባላት በሽብርተኝነት ህግ ላይ ምንም ..... (ከገፅ 1 የዞረ)**

የግንቦት 7 ድምጽ ከአሁን በፊት እንደዘገበው ረቂቅ ህጉ በሰላማዊ የትግል ስትርቴጂ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ማንኛውንም ዓይነት ተቃውሞ በሽብርተኘንት ለመፈረጅ የሚያስችል ድንጋጌ ያለው በመሆኑ በዜጎች መብት ላይ እንዲህ አይነቱን ከፍተኛ ገደብ መጣል በሚችል ረቂቅ ህግ ላይ ዜጎች እንዳይወያዩበት መከልከል የወያኔ ባለሥልጣኖች የሥልጣን እድሜያቸውን ለአንድ ቀንም ቢሆን የሚያራዝም እስከመሰላቸው ድረስ ምን ያህል አፋኝ ድንጋጌዎችን በህዝብ ላይ ለመጫን እንደተዘጋጁ ተጨማሪ ማስረጃ ነው ተብሎአል። ከአሁን ቀደም ይወጡ በነበሩ ሌሎች ረቂቆች ላይ ምንም እንኳን ለውጥ ባያመጡም ለይስሙላም ቢሆን ጋዜጦች ዘገባና ትንታኔ ያቀርቡ እንደነበረ ያስታወሰው የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢ በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገራቸው እንድ አንጋፋ ጋዜጠኛ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል። ፖልስ ኮሚሽኑም ሆነ የደህንነቱ መ/ቤት ሹመኞች መለስ ዜናዊና በረከት ስምኦን አይነቶቹ ፈላጭ ቆራጭ የወያኔ አለቆች የሚያዙትን የሚፈጽሙ ሰለሆነ ለምን አንደሚከለክሉ ሊናገሩ የሚችሉ አይደሉም። በወያኔዎች ቤት የሚሰጠውን ትዕዛዝ ከመፈጸም አልፎ ለምን? ብሎ የምጠይቅ የለም ። እንደወርቅነህ ገበየሁ ዓይነቶቹ በሙስናና በወንጀል የተጨማለቁ የበታች ሹሞች ገና ከጅምሩ ለሹመት ሲታጩ የታዘዙትን እንደሚፈጽሙ ተረጋግጦ ሰልሆነ ለቦታው የሚታጩት ፣ በዚህ ላይ ደግሞ እነርሱ ራሳቸው በሙስናና በተለያየ ወንጀል ውስጥ እንዲነከሩ ተመቻችቶላቸው ስለሆነ የሚያስፈጽሙት ትዕዛዝ ተገቢ እንኳ ባይመስላቸው ተገቢ አለመሆኑን ለማየትም ሆነ ለመጠየቅ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን የሚጎላቸው የመንፈስ ጥንካሬም አይኖራቸውም ብለዋል።

አክለውም “ የፖሊስ ኮሚሽኑና የደህንነቱ መ/ቤት ለይስሙላ ነው እንጂ ዋናውን የአፈና ስትራቴጂ የሚነድፉት መለስና በረከት እንደመሆናቸው እነዚህ በጊዜ ብዛት የአንድ ሳንትም ሁለት ገጽታ እየሆኑ የመጡት ሁለቱ የአገሪቱ ነቀርሳዎች ለህዝባችን ያላቸው ከፍተኛ ንቀት በአደባባይ በቃል ከሚናገሩት በላይ በአንድ ምሽት ተረቀው በፓርላማ ተብየው ፀደቀ እየተባሉ በሥራ ላይ እንዲውሉ እየተደረጉ ባሉት አፋኝ አዋጆች እየተንጸባረቁ ናቸው ብለዋል ። ከአገር ውስጥና ውጭ ከፍተኛ አለም አቀፍ ተቃውሞ እየደረሰብት ፀድቆ በሥራ ላይ ሊተገበር ደፋ ቀና የሚባልለት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና ከአመታዊ ባጀታቸው ከ10 በመቶ በላይ የሚያገኙ ማንኛውንም ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ለመገደብ የወጣው አዋጅ ዋቢ ምስክር መሆኑን ማን ያጣዋል? ሲሉም ይጠይቃሉ አስተያየት የሰጡን ባልሙያ።

በመቀጠልም በተለይ ይህ ሽብረትኝነት ለመቆጣጠር የሚሉት ረቂቅ አዋጅ እየተረቀቀ ያለው በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፎችን መምታት ይቻላል በሚል ስሌት ነው። አንደኛ በኢትዮጵያ ሽብርን የሚታገሉ በመምሰል የጸረ ሽብርተኝነት አጋር መሆንና ከምዕራባውያን የሚገኘው አንዳንድ ፍርፋሪ እንዳይቋረጥ ማድረግ ይቻላል ብለው ያስባሉ። ሁለተኛ ደግሞ ተቃዋሚዎችና ደጋፊዎቻቸው በፍርሃት ተሸብበው እንዲሸማቀቁ ለማድረግ ካልሆነና አላርፍ ካሉ ደግሞ አሸባሪዎች ናቸው ብለው በጅምላ ፈርጀው ሊወስዱአቸው የሚፈልጉአቸውን እርምጃዎች ህጋዊ ሽፋን መስጠት ይቻላል በሚል ስሌት እንደሆነ ያላቸውን ግምት ገልጸዋል።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆነ ቀንደኞቹ አሸባሪዎች መለስና በረከት እንደሆኑ በሚገባ ያውቃል። ከአንዳንድ መንግስታት በስተቀር የአለምአቀፍ ማህበረሰብም ቢሆን መለስ እስካሁን በአገሩ ህዝብና በጎረቤት ሶማሊያ ላደረሰው እልቂት ተጠያቂ መሆን አለበት እያሉ ናቸው። በተለይም በአለም አቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀልን የሚከታተለው ጄኖሳይድ ዎች የሚባለው ድርጅት ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ላይ መለስ ዜናዊና እርሱ የሚመራው ቡድን አስከ አሁን በተለያዩ ጊዜያት በአገራችን ዜጎች ላይ ላደረሱት የዘር ማጥፋትና በሰብአዊ ፍጡር ላይ ለተፈፀመው ሰቆቃ አለም አቀፍ ምርመራ ተደርጎ ለፍርድ እንዲቀርቡ አንድደረግ የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽንን መጠየቁ የሚታወስ ነው።

**የቡድን ሃያ መሪዎች የእርዳታ ገንዘብ የሚዘርፉ አምባገነን .......**
**(ከገፅ 1 የዞረ)**

መለስ ዜናዊ በምን ምክንያት ጋዜጣዊ ጉባዔውን ሰርዞ እንደኮበለለ እንዳልተገለጸ የዘገበው ብላክ እስታር ኒውስ የተባለ የዜና አውታር: የውስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሶ አምባገነኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የሰብዓዊ መብት ጉዳይ፣ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹ ስለሚደረሰባቸው የእንግልት እጣ እና በጎረቤት ሶማሊያ ስለፈጸመው ወንጀል ጥያቄ ይቀርብልኛል ብሎ ፈርቶ እንደሆነ ለንባብ አብቅቶአል።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ያነጋገረቻቸው አስተያየት ሰጪዎች ከምንግዜውም በላይ የመለስ፣ የቤተሰቡ እና የሚመራው መንግስት ባለስልጣናት የዕለት ተዕለት ሃብት ዘረፋ ጉዳይ በግልጽ አደባባይ ላይ እየወጣ ባለብት በዚህን ሰዓት ፣ በድሃ ኢትዮጵያውያን እና አፍሪካውያን ስም ገንዘብ ሊለምን መጥቶ ባለበት እርሱንና መሰሎቹን የሌብነት እርቃን በአጭር ጊዜ ይፋ ሊያድርግ የሚችል ወሳኔ በስብሰባው ላይ መስጠቱ አሰድንግጦት እንደሆነና የምዕርብ አገር ጋዜጠኞች ጥያቄ ሳንሱር የሌለበት መሆኑን ያውቅ ኖሮ ሰለዘረፋው መጠየቁ አይቀሬ መሆኑን በመረዳት ሃፍረት እንደሚከናነብ በማወቁ ፈርቶ ነው ብለዋል።

ብላክ እስታር ኒውስ በዚህ ስብሰባ የአፍሪካ ድምጽ አልተሰማም በሚል በቁጭት ሲናገር፣ የደቡብ አፍሪካው ፕሬዚደንት አፍሪካን ወክለው አለመገኘታቸውን በግልጽ መናገራቸውን ጠቅሶ፣ መለስ ዜናዊን ደግሞ “በፍርሃት ተሸማቆ ተደበቀ” ተመልሶአል ሲል ተችቶታል።

አምባገነኑ መለስ ተቃውሞ የተባለን ነገር ለመቋቋም የሚያስችል በራስ መተማመን ስለሌለው፣ በየጊዜው የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ወደ እስር ቤት እንደሚወረውር በሰፊው ይታወቃል። ቃለ መጠይቅ ሲደረግም ጥያቄውን አስቀድሞ ማጥናት ወይም አዘጋጅቶ መስጠት የለመደው አሰራር እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት የመንግስቱን አሰራር በቅርብ በሚያቁት ሰዎች ተጋልጧል። ተስፋዬ ገብረአብ የተባለው የቀድሞ የወያኔ ባለስልጣን ካጋለጣቸው የውስጥ አሰራሮች ውስጥ አንዱ ይህ ሲሆን፣ መለስን ቃለ መጠይቅ ለሚያደርጉ ጋዜጠኞች ጥያቄ ተዘጋጅቶ ሲሰጣቸው፣ ከሚሰጧቸው ጥያቄዎች አንድም ቃል አዛንፈው እንዳይጠይቁ ከፍተኛ ጫና እንደሚደረግባቸው ገልጿል። በምርጫ 97 ወቅትም ከተቃዋሚ መሪዎች ጋር ክርክርክ ለማድረግ ተስማምቶ የነበረው መለስ ተቃዋሚዎቹ ክርክሩ በቀጥታ እንዲተላለፍ በመጠየቃቸው ቃሉን ማጠፉ ይታወሳል።

አንዳንድ ጊዜ እንደ እድል ሆኖ ከዚህ አይነቱ ቁጥጥር አልፎ ጥያቄ ሲጠየቅ ወደ ዘለፋ እና ማን አለብኝነቱ ዞር እንደሚል በተለያዩ ጊዜያት ፓርላማ ውስጥ በተቃዋሚዎች የሚጠየቁ ጥያቄዎች አጋልጠውታል። በቅርቡ በአንድ የፓርላማ አባል በሶማሊያ ስንት ወታደሮች እንደሞቱ ሲጠየቅ፣ የሞቱ ወታደሮች ቁጥር ፓርላማውን እንደማያገባውና እሱም ለህዝብ ተወካዮች ተብዬዎቹ ተጠያቂነት እንደማይሰማው በመናገር አምባገነንነቱ ጡዘቱ ላይ መድረሱን ማሳየቱ ይታወሳል።

እንደዛ ባልታጠቁ ተቃዋሚዎች ፊት አምበሳ ሊመስል የሚሞክረው መለስ ዜናዊ የአጋዚን ጦር አሰልፎ ለንደን መሄድ ስላልቻለ፣ ካረፈበት ሆቴል ወደ ስብሰባው ቦታ ሲሄድ፥ ከተለያዩ አውሮፓ አገራት የመጡ ኢትዮጵያዉያን አምባገነንነቱን እና ነፍሰ ገዳይነቱን ለዓለም ህዝብ የሚያሳዩ መፈክሮችን ይዘው ሲዘምሩ እና ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ ለማየት ተገዷል። በተጓዘበት መኪና የኋላ ወንበር ወደ ታች ሰጥሞ ቁጭ ብሎ በከሰመ ፊቱ ከመመልከት ውጪ አማራጭ እንዳልነበረው በድህረ ገፆች ላይ የተለጠፉት ፎቶግራፎች አሳይተዋል። ይህ ውርደት ሳያንስበትም፥ የእንግሊዝ አገር እና አንዳንድ አለማቀፍ የዜና አውታሮች የኢትዮጵያዉያኑን የተቃውሞ ሰልፍ በቴሌቪዢን መስኮታቸው በማሳየት የመለስ ዜናዊን የነፍሰ ገዳይነት ዝና የባሰ አጉልተውታል።

ይህንን ሁሉ ሃፍረት ከተከናነበ በኋላም፥ ያለው ኢትዮጵያ እንዳልሆነና ተሰብስበው የሚጠብቁትን ጋዜጠኞች ጥያቄያችሁን መጀመሪያ ካላየሁት ወይም እኔ የማልወደውን ጥያቄ ከጠየቃችሁኝ ከአገር አስወጣችኋለሁ ብሎ ማስፈራራት እንደማይችል ብልጭ ሲልለት ጋዜጣዊ ጉባዔውን ለመሰረዝ ተገዷል።


## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

### የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን

በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።

g7radio@ginbot7.org